# ፍኖተ ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ግንቦት 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 77


## አንድነት ፓርቲ የሰኔ አንድ ሰማዕታትን በህዝባዊ ንቅናቄ ሊዘክር መሆኑን ታወቀ



2

## ደርግን በደርግ የተካው ግንቦት20

ዳዊት ሰለሞን

6

## ወደ ዘዋይ የተወሰዱት የፖለቲካ እስረኞች አያያዝ አስጊ እንደሆነ ተጠቆመ

7

## የአንድ ማህበር ሁለት ድምጾች

4

“ለአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ነው፡፡ ማህበሩ ጠይቆ የሚያጣው አዳራሽ ሆነ በጀት የለም፡፡”

ወጣት ወይንሸት ስለሺ በቅርቡ ከታገዱት የአ.አ ወጣቶች ማህበር የምክር ቤት አባላት መካከል

“የምንተዳደረው በራሳችን ወጪ ነው፡፡ አምስት ሳንቲም የሚረዳን የልም፡፡ መንግስትም የሚያደርግልን የበጀት ድጋፍ የለም”

ወጣት ባህሪዲን አወል የአ.አ ወጣቶች ማህበር ም/ሰባሳቢ

## ጸረ ሙስና የዝቋላ ብረታ ብረት ፋብሪካን አስተዳደር በምክር ማለፉ አነጋጋሪ ሆኗል

8

-‹‹በ2.5 ሚልዮን ዮሮ የተገዛ ማሽን ያለ አገልግሎት ተቀምጧል›› ጸረ ሙስና ኮሚሽን

- ‹‹ጸረ ሙስና ስለ እኛ ሪፖርት ማቅረቡን አናውቅም››የፋብሪካው አስተዳዳሪ አቶ ጥበበ አየለ

## የአፍሪካ ህብረት የአምባገነኖች መሰባሰቢያ መሆኑ ይብቃ

2

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

ፍኖተነፃነትጋዜጣሐምሌ2003ዓ.ምተመሰረተ።

ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ።

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው። ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን። ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው።

## ርእሰ አንቀጽ

# የአፍሪካ ህብረት የአምባገነኖች መሰባሰቢያ መሆኑ ይብቃ

ይህ ወቅት የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የአፍሪካ ህብረት 50ኛ አመት የሚያከብርበት ነው። የዛሬ 50 አመት ኢትዮጵያን ጨምሮ በጊዜው ነፃነታቸውን ያረጋገጡ የአፍሪካ ሀገሮች በመዲናችን አዲስ አበባ በመሰባሰብ የመሰረቱት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከ11 አመት በፊት ወደ አፍሪካ ህብረት ተሸጋግሯል። በፓን አፍሪካዊ አስተሳሰብ የተፀነሰው ይኸው ተቋም አፍሪካውያንን ከቅኝ ግዛትና ከባርነት አላቆ የበለፀገች አፍሪካን የመፍጠር አላማ ነበረው።

ተቋሙ የተመሰረተበትን 50ኛ አመት ሲያከብር ሁሉም የአፍሪካ ሃገራት ከቅኝ ግዛት ነፃ ቢሆኑም እንደተቀሩት የአለም ክፍሎች በዴሞክራሲና በኢኮኖሚያዊ እድገት ረገድ አብዛኞቹ ሀገራት ወደኋላ መቅረታቸው ሊያሳስብ ይገባል። የኋላቀርነቱ ምንጭ የሆነው ለዘመናትበአፍሪካ ህዝቦችላይ ተጭኖ የቆየው አምባገነናዊ አገዛዝ ስለመሆኑ ነጋሪ አያሻውም። የአፍሪካ ህብረት ከአህጉሪቱ አንባገነናዊ አገዛዝ እንዲወገድና አፍሪካውያን ከባርነት ነፃ እንዲወጡ ባለፉት ዘመናት ምንም ለማድረጉ በታሪክ ተወቃሽያ ደርገዋል።ህብረቱ የአባል ሀገራት መንግስታት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲያደርጉ ማበረታታት ይጠበቅበታል። በመፈንቅለመንግስት ስልጣን የሚይዙ መንግስታትን እንደሚያግደው ሁሉ፣ በተጭበረበረ ምርጫ ስልጣን የሚይዙ መንግስታትን ከህብረቱ በማገድም አህጉሪቱን የተረጋጋችና ከፖለቲካዊ ቀውስ የፀዳች እንድትሆን የበኩሉን በወጣት አለበት። ቢሞላውም ሊያሳካ ያለመውን

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት ኢትዮጵያ የነፃነት ምሳሌ ነበረች። አሁን ግን እንደአብዛኞቹ አፍሪካውያን ኢትዮጵያውያንም በአምባገነናዊ ባርነት ስር ሆነን የአፍሪካ ህብረትን 50ኛ አመት ማክበራችን ሊያስቆጨን ይገባል። ከሀምሳ አመት በፊት በነጭ ወራሪዎች ግዛት ስር ሆነው በባርነት ይኖሩ የነበሩት አፍሪካውያን ዛሬም በአምባገነን መንግስታት ባርነት ስር መሆናቸው መላውን አፍሪካውያን ሊያሳስብ ይገባል። ሁሉንም ወገን ሊያስማማ የሚችለው የባርነት ፍቺ ‹‹የራስ ፈቃድ ሳይኖር ያለፍላጎት የገዢን ፍላጎት እየፈፀሙ መኖር›› የሚል ነው። በዚህ ፍቺ መሰረት በባዕዳንም ሆነ በሀገሬው ገዢዎች ባርነት ስር መውደቅ የቅርፅ እንጂ የይዘት ለውጥ የለውም። በመሆኑም አፍሪካውያን አሁንም ከባርነት በመውጣት ዴሞክራሲያዊ ነፃነታቸውን አግኝተው በራሳቸውና በሀገራቸው ጉዳይና ጥቅም ላይ ቀጥተኛ ወሳኝነት እንዲኖራቸው በጥንካሬ መታገል አለባቸው። የአፍሪካ ህብረትም ይህን ትግል የመደገፍ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም የሰነቀው አፍሪካውያንን ሁሉ የነፃነት ተቋዳሽ የማድረግ አላማ ተሳክቷል ብሎ ለመናገር ድፍረት ያሳጣል። ምክንያቱም አፍሪካውያን በቅኝ ግዛት ወቅት ይደርስባቸው የነበረው ብሔራዊ ጭቆና፣ አፈና እንዲሁም የሀብት ዝርፊያ አሁንም በሚገዙዋቸው አምባገነን መሪዎች እየተፈፀመባቸው ነው። አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት በጦር መሳሪያ እና በተጭበረበረ ምርጫ ስልጣን ላይ በወጡ

አምባገነን ገዢዎች ስር ናቸው። አፍሪካውያን የሀገራቸውን ሀብት በውጭ ወራሪዎች ከመበዝበዝ ቢድኑም አምባገነን ገዢዎቻቸው በከፍተኛ መጠን እየዘረፏቸው ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በጥቂት አመታት ውስጥ ብቻ አስራ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር በላይ በኢህአዴግ ባለስልጣናት ተዘፍፎ በህገወጥ መንገድ ከሀገር እንደወጣ በአለም አቀፍ ተቋማት ተረጋግጧል። ይህ አይነቱ ዝርፊያ በሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራትም እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የነፃነት ጥያቄ ባነሱ አፍሪካውያን ላይ ቅኝ ገዢዎች ያደርሱ ከነበረው ግድያ ባልተናነሰ ሁኔታ የአሁኖቹ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች የጅምላ ግድያ ይፈፅማሉ።

የአፍሪካ ህብረት የአምባገነኖች መሰባሰቢያ መሆኑን የአፍሪካውያንን ሁሉ የሚያሳስብ በመሆኑ እኛንም ያሳስበናል። የዛሬው መልዕክታችንም ‹‹የአፍሪካውያን የነፃነት ጥያቄ ይሰማ! የአፍሪካ ህብረት የአምባገነኖች መሰባሰቢያ መሆኑ ይብቃ!›› የሚል ነው።

ጋዜጣችንን “ፍኖተ ነፃነት“ ብለናታል “ፍኖት“ ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው::

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# አንድነት ፓርቲ የሰኔ አንድ ሰማዕታትን በህዝባዊ ንቅናቄ ሊዘክር መሆኑን ታወቀ



አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የግንቦት 97ን ምርጫ ተከትሎ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በመንግስት ሀይሎች በግፍ የተጨፈጨፉትን ኢትዮጵያውያን ለመዘከር የተለያዩ ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆኑን ለፍኖተ ነፃነት የደረሰው መረጃ አመላክቷል፡፡

ፓርቲው በአዲስ አበባ መዋቅሩ ጭፍጨፋው የተፈፀመበትን እለት በህዝባዊ ንቅናቄ ለመዘከር ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የፓርቲው የአዲስ አበባ ዞን ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ትዕግስቱ አወሉ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

አቶ ትዕግስቱ እንደተናገሩት የህዝባዊ ንቅናቄውን በበላይነት የሚመራው የአዲስ አበባ ዞን ምክር ቤት ነው፡፡ ሰብሳቢው ጨምረው እንደገለፁት ዝግጅቱን የሚያስተባብር ኮሚቴ ተዋቅሮ ዝርዝር አፈጻፀሙን በማዘጋጀት በቅርቡ ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

**በውጭ ሀገር ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ የህትመት መሳሪያ ማደራጃ ለመግዛት እንዲቻል ጥሪ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ በጥሪው መሰረት በርካታ ወገኖቻችን ተግባራዊ ምላሽ እየሰጡ መሆናቸው በወገኖቻችን እንድንኮራ አድርጎናል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ወገኖቻችን በገንዘብ አላላኩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመጠየቃቸው ይህን ማብራሪያ አቅርበናል፡፡ ገንዘቡ የሚገባው በቀጥታ በፍኖተ ነጻነት አካውንት ነው፡፡**

1/በኦንላይን እርዳታ ለማድረግ ለምትፈልጉ በፔይፓል (pay pal secure payment)
እነዚህን ድህረ ገጾች ይጎብኙ

http://www.fnotenetsanet.com/
http://www.andinet.org/
http://www.andinetusa.org/

2/ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ ለምታስተላልፉ

Andinet North America (Finote Netsanet News Paper)
Bank Name : Wells Fargo
ACC# 753-085-0978
Routing # 054-001-220

3/ በቼክ ወይም በገንዘብ ማዘዣ (money order)

Andenet North America (Finote Netsanet News Paper)
P.O.Box 48355
Washington DC 20002
Tel. (202) 462-0556 Fax: (202) 462-0557

ማሳሰቢያ ፡ ገንዘቡን ገቢ ካደረጋችሁ በሁዋላ በሚቀጥለው ኢሜይል አድራሻ ብታሳውቁን ለስራችን ጥራት ይረዳናል፡፡
Email: info@andinetusa.org
ስለትብብራችሁ አስቀድመን ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡
በመላው አለም የምትገኙ ወገኖቻችንም ይህን መረጃ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በሰሜን አሜሪካ

**ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67**

# የአንድ ማህበር ሁለት ድምጾች

## የዛሬ እንግዶቻችን ወጣት ወይንሸት ስለሺ እና ወጣት ባህረዲን አወል በውዝግብ እየታመሰ የሚገኘው የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር አባላት ናቸው።

**“ለአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ነው። ማህበሩ ጠይቆ የሚያጣው አዳራሽ ሆነ በጀት የለም።”**

ወጣት ወይንሸት ስለሺ በቅርቡ ከታገዱት የአ.አ ወጣቶች ማህበር የምክር ቤት አባላት መካከል

ፍኖተ ነፃነት፡- የአዲስ አበባ ወጣቶች አመሰራረት እንዴት ነበር?

ወይንሸት፡- የአዲስ አበባ ወጣቶች ከተመሰረተ 15 ዓመተታት ያህል ተቆጥረዋል። በእነዚህ ጊዜያቶች ምን ሰራ የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ቢሆንም ማህበሩ የተመሰረተው ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወገንተኛ ሳይሆን ወጣቱን በሚመለከቱ ፖለቲካዊ ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገርና በመታገል መብታቸውን ለማስከበር በሚል መነሻ ነበር ።

ፍኖተ ነፃነት፡- ማህበሩ ሲመሰረት ደንብ ነበረው?

ወይንሸት፡- በአዲስ አበባ የሚገኙ ወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለየትኛውም የፖለቲካ ሃይል ሳልወግን በነጻነት በመደራጀት ህልሜን አሳካለሁ የሚል ርዕይ ነበረው። የተመሰረተውም በዚህ ማዕቀፍ ነው።

ፍኖተ ነፃነት፡- ማህበሩ ከምስረታው ጀምሮ ከኢህአዴግ የተለየ አቋም የነበራቸውን የአዲስ አበባ ወጣቶች ባለማቀፉ በነጻነቱ ዙሪያ የወጣቱን እምነት አላገኘም…

ወይንሸት ፡- ትችቱ ከባዶ ሜዳ የተነሳ አይደለም። ለይስሙላ ነጻ የሲቪክ ማህበር ተብሎ ፈቃድ ያገኘ ቢሆንም የገዢው ፓርቲ ተለጣፊ ለመሆኑ ብዙ ምርምር ማድረግ አያስፈለግም። ለምሳሌ በአንድ አጋጣሚ እንኳን ማህበሩ ከመንግስት ወይም ከገዢው ፓርቲ የተለየ አቋም ሲያራምድ ታይቶ አይታወቅም። የሚሰራው ከላይ ከኢህአዴግ ጽ/ቤት የወረደለትን እንጂ በራሱ መንገድ አይደለም። በአጠቃላይ ማህበሩ የገዢውን ፓርቲ ተልእኮ ለማሳካት የሚሰራ እንጂ የራሱ የሆነ ተልእኮ ያለው ማህበር አይደለም።

ፍኖተ ነፃነት፡- ማህበሩን የተቀላቀልሽው መቼ ነበር? በማህበሩ ውስጥ ያለሽስ ሃላፊነት ምንድን ነው?

ወይንሸት፡- ማህበሩን የተቀላቀልኩት በ2002 መጀመሪያ ሲሆን የጉለሌ ክፍለ ከተማ ገንዘብ ያዥና የጸሀፊ ነበርኩ ። በክፍለ ከተማው እየሰራሁ በነበረበት ሁኔታ አመራሮቻችን በቀጥታ ከኢህአዴግ ጽ/ቤት የመጣውን ስራ እንድንሰራ ያስገድዱን ነበር ። ለምሳሌ በማህበር ውስጥ ያሉ አባላትን በተለያየ ቡድን አደራጁ ይሉ ነበር። ይህንን ግዳጅ “ፍራክሽን” በማለት ይጠሩታል። በፍራክሽን የሚደራጁት ደግሞ የማህበራችን አባላት ሆነው በኢህአዴግ ሊግ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ናቸው። የማህበራችን አባላት ሆነው የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ወይም አባላት የሆኑ ግን በፍራክሽን እንዲደራጁ አይፈቀድላቸውም። በፍራክሽን ከተደራጁት የሊግ አባላት ደግሞ ማህበራችን ልምድ ይቅሰም አመራርም ይቀበል ተባለ። ፍራክሽን የሚባለው ነገር የኢህአዴግን ወጣቶች ሊግን ከመጥቀም ውጪ ለእኛ የሚፈይደው ነገር የለም በማለት ተቃውሞ ማሰማታችን ብዙ ነገር አምጥቶብናል። ሌላው በተለየያዩ የአክራሪነት ስራዎች እንድንሳተፍ ያስገድዱን ነበር።

ፍኖተ ነፃነት፡- የአክራሪነት ስራ ማለት?

ወይንሸት፡- የማህበሩ አባል ላልሆነ ሰው ፍራክሽንና አክራሪነት የሚሉት ቃላት ግልጽ

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

**“የምንተዳደረው በራሳችን ወጪ ነው። አምስት ሳንቲም የሚረዳን የልም። መንግስትም የሚያደርግልን የበጀት ድጋፍ የለም”**

ወጣት ባህረዲን አወል የአ.አ ወጣቶች ማህበር ም/ሰባሳቢ

ፍኖተ ነፃነት፡-- በቅርቡ ለምታደርጉት ጠቅላላ ጉባዔ ‹‹ በመለስ ሌጋሲ የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ›› የሚል መሪ ቃል መርጣችኋል።ማህበሩ ነጻ ማህበር ነኝ እያለ እንዲህ አይነት መሪ ቃል መምረጡ ለፍረጃ ቅርብ አያደርገውም?

በህረዲን --መሪ ቃሉን ዝም ብለን አልመረጥነውም ብዙ ከተነጋገርንና ከተያየን በኋላ ነው የመረጥነው።ብዙ መሪ ቃሎች ቀርበው ተወዳድሮ ነው ይህ በመጨረሻ የተመረጠው። እንደሚታወቀው ይህ መሪ ቃል ከመመረጡ በፊት ትችት ቀርቦበት ነበር ነገር ግን የአብላጫውን አባል ድምጽ በማግኘቱ ለመመረጥ በቅቷል።

ፍኖተ ነፃነት፡-- መለስን እንዴት ልትመርጡ ቻላችሁ ; ለወጣቱ አርአያ መሆን የሚችሉ ብዙ ኢትዮጵያዊያኖች እንዳሉ ይሰማናል፣ከእነዚህ በመለየት መለስን የመረጣችሁበት ምክንያት ምንድን ነው፣ መለስስ ለወጣቱ አርአያ የሚሆኑበትና ወጣቶቹ የእርሳቸውን ሌጋሲ(ውርስ) የሚያስቀጥልበት መነሻ ምንድን ነው?

ባህረዲን፡- ክርክሮች እኛም ጋር ተነስተዋል፣መለስ በወጣትነቱ በረሀ ገብቶ መብቱን ለማስከበር ታግሏል ስለዚህ እኛም መብታችንን ለማስከበር መታገል እንደሚገባን (ይህንንም ስርዓት ቢሆን)ትልቅ ትምህርት የሰጡን በመሆኑ አርአያችንነ አድርገናቸዋል

ፍኖተ ነፃነት፡- መለስን ግን ብዙዎች ከሰላማዊ ትግል ይልቅ ብረት ማንሳትን ያስተማሩና አፋኝ ያሉትን ስርዓት ከጣሉም በኋላ ቢሆን ስልጣናቸውን ላለማጣት ወጣቶችን በአደደባባይ በጥይት እንዳስደበደቡ በመግለጽ አርአያ መሆን እንደማይችሉ ይሞግታሉ…

ባህረዲን ፡- ሁሉም ሰው ድካም የለበትም ማለት አይቻልም መለስም አርአያ ሊያደርጓቸው የሚችሉባቸው ስራዎች እንዳሏቸው ይሰማኛል። በአጠቃላይ ግን ይህንን መሪ ቃል የመረጥነው ተነጋግረንና ሌሎች መሪ ቃሎችን ከተመለከትን በኋላ ነው።

ፍኖተ ነፃነት፡-- እስኪ ለውይይት ቀርበው ነበር የምትላቸውን መሪ ቃሎች ንገረን?

ባህረዲን፡- ‹‹ሁሌም እንሰራለን እንለወጣለን››‹‹መደራጀታችን በፍላጎታችን››የሚሉ ነበሩ።

ፍኖተ ነፃነት፡-- ልክ እንደ አዲስ አበባ ወጣትማህበር ሁሉ የኢህአዴግ ወጣት ሊግም ተመሳሳይ የሆነ መሪ ቃል መርጧል ይህስ በእናንተና በኢህአዴግ ሊግ መካከል ልዮነት እንደሌለ ማመላከቻ አይሆንም?

ባህረዲን -- እንደዚህ ሊል የሚችል ሰው ይኖራል።እኛ ይህንን መሪ ቃል የመረጥነው ከተወያየንና ከተነጋገርን በኋላ ነው። የጠቅላላ ጉባዔው ንዑስ ኮሚቴ የተለያዩ መሪ ቃሎችን በማምጣት እንድንወያይ አድርጋዋል በመጨረሻም ‹‹ በመለስ ሌጋሲ የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ››የሚለው ተመርጧል።

ፍኖተ ነፃነት፡-- ባህረዲን በአጭሩ ማህበራችን የየትኛውም ፖለቲካ ድርጅት ጥገኛ አይደለም እያልከኝ ነው?
ባህረዲን፡- ነጻነታችንን በተመለከተ ለማወቅ የምንሰራውን ስራ ማየት ይበቃል።ዝም ብዬ እኔም እንዲህ

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

## ለአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር መንገዱ ሁሉ አልጋ . . . ከገፅ 4 የዞረ

ላይሆንለት ይችላል፡፡ አክራሪነት የሚለው ስራ የአገራችን ሙስሊሞች ያነሱትን ጥያቄ ለማፈን የሚሰራ ስራ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ይህንን እንቅስቃሴ ለመምታት አባላቱ በየቀበሌው በሚገኙ ሙስሊሞች ቤት በመግባት የእንቅስቃሴው አካል እንዳይሆኑ ያግባባ ነበር ፡፡ በእርግጥ ግጭት እንዳይፈጠር በሰላማዊ መንገድ የተነሱ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ማህበሩ የሽምጋይነት ሚና የሚጫወትበት ቢሆን ሁላችንም ደጋፊ እንሆን ነበር ነገር ግን ተልእኮው ይህ አልነበረም፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- በቅርቡ ማህበሩ ባደረገው ስብሰባ አንቺን ጨምሮ ከ20 የማያንሱ አመራሮችን ማገዱን ሰምተናል፡፡ የእግዱ ምክንያት ምን ነበር?

ወይንሸት፡- በየክፍለ ከተማው ከስብሰባው ቀደም ብሎ ግምገማ ተደርጎ ነበር፡፡ የግምገማውን ውጤት በመንተራስ ደግሞ በከተማ ደረጃ ስብሰባ ተደርጓል፡፡ ግምገማው በዋናነት የማህበሩን ነጻነት በማስጠበቅ ስለ ተሰራ ስራ ሳይሆን ከማዕከል የወረደውን ስራ ስለመፈጸም ነበር፡፡ በዚህ ደግሞ እኛ እንደሌሎቹ የወረደውን ብቻ በመቀበል የምንታዘዝ ባለመሆናችን እንድንታገድ ተደርገናል፡፡ በከተማ ምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት አንዱ አባል ተነስቶ ‹‹እኔ ለምሳሌ የሙስሊም ልብስ ለብሼ መስጊድ በመግባት ብዙ ስራ ሰርቼያለሁ እናንተ ግን ምን ሰራችሁ›› እያለ ሊወቅሰን ሞክሮ ነበር፡፡ እኔ የአክራሪነትን ስራ ለመስራት እንዲህ ማድረግ የሚገባኝ አይመስለኝም፡፡ ወደ ማህበሩ የገባሁት እንዲህ አይነት የወረደ ስራ ለመስራት አይደለም፡፡ እኛ ማንንም ለመሰለል የማህበሩ አባል አልሆንም፡ ፡ ስለዚህ ከመነሻው እነርሱ አገድናችሁ አሉን እንጂ ቀድመን መልቀቂያ አቅርበን ነበር፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር በህግ የተሰጠው ፈቃድ የነጻ ሲቪክ ማህበር የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በግልጽ የአንድ ፓርቲ ክንፍ ሆኖ እየሰራ ይገኛል፡፡

ወይንሸት፡- ብዛት ያላቸው ሲቪክ ማህበሮቶች በአሁኑ ሰዓት መንቀቀሳቀስ አልቻሉም ፡ ፡ በቅርቡ የወጣው የሲቪክ ማህበራት አዋጅ የማህበራቱን ህልውና አጣብቂኝ ውስጥ እንደከተተው ጸሐይ የሞቀው ሀቅ ነው፡፡ ነገር ግን ለአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ነው፡፡ ማህበሩ ጠይቆ የሚያጣው አዳራሽ ሆነ በጀት የለም፡፡ በቀበሌ ደረጃ ከሚገኙ አዳራሾች ጀምረህ ለማህበሩ የሁሉም በር ክፍት ነው፡፡መቼም እንዲህ አይነት ነገር ነጻነቱን ጠብቆ ለሚኖር ማህበር የማይታሰብ እንደሆነ ሁሉም ያውቃል፡ ፡ ለምሳሌ በዚህ ወር መጨረሻ ማህበሩ ለሚያደርገው ጠቅላላ ጉባዔ ከመንግስት አንድ ሚልዮን ሶስት መቶ ብር ወጪ ተደርጓል፡ ፡መንግስት ይህንን ገንዘብ ከየት ያመጣል? የአንተ የእኔና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ገንዘብ ነው፡፡ ለምን ለማህበሩ ይህ ገንዘብ ተፈቀደ? ለዚያውም የሚበዛውን ወጣት የማይወክል ማህበር ለሚያደርገው ጉባዔ ይህንን ያህል ገንዘብ መበጀቱ የማህበሩን ማንነት ወለል አድሮ የሚያሳይ ነው፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- ገንዘቡን ለማህበሩ የለቀቁ ድርጅቶች ገንዘቡን እንዲያዋጡ ትዕዛዝ ወርዶላቸው ነው?

ወይንሸት፡- አዲስ አበባ ወጣቶች ማህበርን በገንዘብ የደጎሙ መንግስታዊ ድርጅቶች ድጋፉን ያደረጉት እንደተባለው የማህበሩን እንቅስቃሴ ገምግመው ቢሆን ኖሮ ማንም ተቃውሞ አያሰማም፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ማህበሩ የገዢው ፓርቲ ድጋፍ ያልተለየው በመሆኑ የሚጠይቀው ሁሉ እንዲሟላለት ይደረጋል፡፡ ገንዘቡን ለማህበሩ ከሰጡ ድርጅቶች መካከል የሴቶች የህጻናትና የወጣቶች ጽ/ቤት አንዱ ነው ድርጅቱ ከሃያ ሺህ ብር በላይ ለግሷል፡፡ ይህ ገንዘብ የስንቱን ህጻን ፍላጎት ይሞላ ነበር

ፍኖተ ነፃነት፡- የባለ ራዕይ ወጣቶች ስብሰባ ለማድረግ ለሆቴል ከፍለው ሲከለከሉ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር በነጻ አዳራሽ ተፈቅዶለት ለአባላቱ አበል ተቆርጦለት ስብሰባውን ያከናውናል፡፡ በሁለቱ ማህበራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው?

ወይንሸት -- ልዩነቱ የማንነት ነው፡፡ ባለራዕይ ማህበር ውስጥ ያሉ ወጣቶች ተላላኪዎች አይደሉም፡፡ባለመላካቸው ደግሞ የሚከፍሉት ዋጋ ይኖራል፡፡

ፍኖተ-- በወሩ መጨረሻ የአዲስ አበባ ወጣት ማህበር ለሚያደርገው ጠቅላላ ጉባዔ መሪ ቃል መርጧል‹‹የመለስን ሌጋስ ማስቀጠል ለወጣቱ ተጠቃሚነት››ይላል መሪ ቃሉ፡፡ ይህንን መሪ ቃል የጠቅላላ ጉባዔው አባላት ተነጋግረው የመረጡት ነው? እንዴትስ አንድ ነጻ ነኝ የሚል ማህበር የገዢው ፓርቲ ክንፍ መሆኑ ከሚታወቅለት የኢህአዴግ ወጣት ሊግ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መሪ ቃል ሊመርጥ ይችላል?

ወይንሸት፡- በጣም የሚገርመኝ እንደውም በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት መሪ ቃሉ ሲነገር የሚበዙት ወጣቶች ተቃውመው ነበር፡፡ ማህበሩ የራሱ ሌጋሲና ራዕይ ሊኖረው ሲገባ የመለስን ሌጋሲ አስቀጥላለሁ ማለቱ ወዴት እየሄደ እንደሚገኝ ግልጽ ማሳያ ነው፡፡ መለስን በግሉ የሚያደንቀው፣የሚደግፈው የፈለገውን ሊናገርና ሊያደርግ ይችላል፡፡ የመለስን ሌጋሲ ማስቀጠል አልፈልግም የሚል ወጣትስ ምን ሊያደርግ ነው፡፡ይህ ማህበርስ በምንሞራል ነጻ ነኝ በማለት መናገር ይችላል፡፡

## የምንተዳደረው በራሳችን ወጪ . . . ከገፅ 4 የዞረ

ነው እንደዚያ ነው ማለት አልችልም ጠጋ ብሎ የምንሰራውን መመልከት ይገባል፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡-- ለምሳሌ በጀት የሚያደርግላችሁ አካልየሚፈልገው ነገር ይኖራል፣ በተጨማሪም አሁን ለምታደርጉት ጠቅላላ ጉባዔ መንግስታዊ ከሆኑ ድርጅቶች ወደ አንድ ሚልዮን ሶስት መቶ ብር ተለግሷችኋል፣የምትፈልጉትን አዳራሽ በነጻ ታገኛላችሁ፣እንደምታውቀው በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የሲቪክ ማህበራት በአጣብቂኝ ውስጥ ይገኛሉ ለእናንተ ግን መንገዱ አልጋ ባልጋ ሆኖላችኋል ከዚህ አንጻር ነጻነን ማለታችሁን ጥያቄ ውስጥ መክተት ያስቸግራል?

ባህረዲን፡- በጀታችን ከየትም የሚመጣ አይደለም ፣ የምንተዳደረው በራሳችን ወጪ ነው፡፡ አምስት ሳንቲም የሚረዳን የልም፡ ፡ መንግስትም የሚያደርግልን የበጀት ድጋፍ የለም ፣አንዳንድ ጊዜ ግን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ስናቀርብ ድጋፍ ይደረግልናል ፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡-- እናንተ እያገኛችሁት ያለውን አይነት ድጋፍ ሌሎች ለምን አያገኙም;ለምሳሌ የሴቶችና ህጻናት ጽ/ቤት በጥሬ ሃያ ሺህ ብርና አስር ሺ ቲሸርቶችን ከእነ ኮፊያቸው እንደሰጣችሁ ይታወቃል፡፡እና ይህ ድጋፍ ማህበር ስለሆናችሁ ብቻ የተገኘ ነው?

ባህረዲን--ከሴቶችና ህጻናት ጋር በደንብ እየሰራን እንገኛለን ፡፡ደግሞም እኮ መንግስታዊ ተቋማት እኛን መደገፍ ግዴታቸው ነው፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡-- ማነው ግዴታ ያደረገባቸው;

ባህረዲን -- ስራቸውን እየሰራንላቸው የምንገኝ በመሆኑ መርዳት አለባቸው፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡--  ልክ እንደ እናንተው ባለ ራዕይ ወጣቶች የተሰኘ ማህበር አለ ፣ይህ ማህበር ስብሰባዎችን ለማድረግ አዳራሽ ተከራይቶ አባላቱን ከጠራ በኋላ ስብሰባው እንዲቋረጥ ተደርጎበታል፣የማህበሩ አባላት መሰብሰቢያ በማጣት ስብሰባቸውን ማከናወን አልቻሉም ወደ እናንተ ስንመጣ ግን የሁሉ በር ክፍት ይሆንላችኋል፡፡ይህንንስ እንዴት ታየዋለህ?

ባህረዲን -- ለእኛም መንገዱ ከጥቂት አመታት በፊት እንዲህ አልነበረም፡፡ አዳራሽ የተከለከልንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡ ፡ በነጻም አዳራሽ ተጠቅመን አናውቅም ፡ ፡ሌላው ስብሰባ ሲኖረን አንድ ቦታ ብቻ አንጠይቅም ብዙ ቦታ ስለምንሞክር አንዱ ጋር ይሳካልናል፡፡መደበቅ የማይቻለው ነገር ደግሞ ማህበሩ ከፍተኛ የሆነ የገጽታ ገንብተናል፡፡ ይህም በጣም እየጠቀመን ይገኛል፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡-- የመንግስትንና የተቋማቱን እምነት በምን ማግኘት ቻላችሁ?

ባህረዲን--ለምሳሌከተማእናስውባለን፣በተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንሳተፋለን ይህንን ማድረጋችን ተቀባይነታችንን ጨምሮልናል፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# ደርግን በደርግ የተካው ግንቦት 20

ዳዊት ሰለሞን

**በአስራ ሰባት መርፌ**
**በጠቀመው ቁምጣ**
**ለለውጥ ያጎፈረው**
**ስልጣን ላይ ቢወጣ**
**አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ**
**(ቴዲ አፍሮ)**

ግንቦት 20/1983 በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ የተደረገበት በመሆኑ ቀኑ በአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያሳደረውና በሂደትም የሚያሳድረው ተጽእኖ ለውጡን በፈጠሩት አካላት ዲስኩር ብቻ ተተንትኖ ያበቃል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ለውጡን የማይደግፉትና በለውጡ አቀንቃኞች ‹‹የቀድሞው መንግስት ናፋቂዎች›› የሚሰኙት ጭምር በአንድም በሌላም መንገድ ቀኑ ይነካቸዋልና ድምጻቸውን ሊያሰሙ ይገባቸዋል፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከ1984 ግንቦት ሃያ ጀምሮ ስለ ቀኑ እንዲናገሩ ሰፊ የአየር ሰዓት የሚቸራቸው ለተጋዳላዮቹ ብቻ ነው፡፡

ተጋዳላዮቹ በበኩላቸው ስለ ግንቦት ሃያ ሲያወሩ በዋናነት ማተኮር የሚፈልጉት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ስላሳለፉት የበረሃ ህይወት ነው፡፡ እስከ አፍኛጫው ታጥቆ የነበረ የሚሉትን ደርግን ስለ ተፋለሙባቸው ውጊያዎች፣የጦር ሜዳ ጀብዱዎች ይተርካሉ፡፡ ጠላትን ለመግደል ስለ ፈጸሙት ጀብድ ሲያወሩ ግን ማን እንደሚሰማቸው እንኳን የሚጨነቁ አይመስሉም፡፡ ለ17 ዓመታት የተደረገው ጦርነት በወንድማማቾች መካከል በመሆኑም የያኔዎቹ ታጋዮች ግዳይ መጣላቸውን ሲያወሩ ባሏን በሞት የተነጠቀች እመበለት፣ልጇን ያለ ውዴታው ያጣች እናት፣አባታቸውን ለጦርነቱ የገበሩ ልጆች በቴሌብዥን መስኮት ያደምጧቸዋል፡፡ በየዓመቱ ግንቦት ሃያ በመጣ ቁጥር እነዚህ ቤተሰቦች ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ማሰብ ህመም ይፈጥራል፡፡

‹‹አገር ለመገንጠል ወንበዴዎች ተነስተዋል›› በሚለው የደርጉ የእናት አገር ጥሪ መሰረት የዘመቱ ወታደሮች የደርግ ተብለው በየግንቦት ሃያው‹‹ጠላት››እየተባሉ መጠቀሳቸው በጦርነቱ መንስዔ አካላቸውን ላጡ ሁሉ ከህሊና የማይሽር ጠባሳ ነው፡፡

ኢህአዴግ ግንቦት ሃያን በማስመልከት ለህዝቡ የሚያሰራጫቸው ፕሮፓጋንዳዎች ሁለት ጫፍ የረገጡ ናቸው፡፡ ፕሮፓጋንዳዎቹ ለምን አላማ እንዲውሉ ታስበው ድርጅቱ እንደመንግስት በተቆጣጠራቸው ሚዲያዎች እንደሚያሰራጫቸው ማሰብም ገዢውን ፓርቲ ከግንቦት ሃያ በፊት ከነበረበት የጫካ አስተሳሰቡ አለመላቀቁን ለመታዘብ ያስችለናል፡፡

ገዢው ፓርቲ ወደ ምኒልክ ቤተመንግስት ከገባ 22 ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ድርጅቱን ለዚህ ያበቁት ተጋዳላዮችም በአሁኑ ሰዓት በእድሜና በተለያየ ምክንያት ከጨዋታ ውጪ እየሆኑ ነው፡፡ ድርጅቱ አዳዲስ

ለ17 ዓመታት የተደረገው ጦርነት በወንድማማቾች መካከል በመሆኑም የያኔዎቹ ታጋዮች ግዳይ መጣላቸውን ሲያወሩ ባሏን በሞት የተነጠቀች እመበለት፣ልጇን ያለ ውዴታው ያጣች እናት፣አባታቸውን ለጦርነቱ የገበሩ ልጆች በቴሌብዥን መስኮት ያደምጧቸዋል፡፡ በየዓመቱ ግንቦት ሃያ በመጣ ቁጥር እነዚህ ቤተሰቦች ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ማሰብ ህመም ይፈጥራል፡፡

ፊቶችን በተወሰነ ደረጃ እያሳየን የሚገኝ ቢሆንም አዲስ ፊቶቹ በቀድሞዎቹ ( old guareds )መንገድ ግነቦት ሃያን እያከበሩ ይገኛሉ፡፡

በግንቦት ሃያ ክብረ በዓል ከሚቀርቡልን ዲስኩሮች መሃል የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የጦርነቱ ታሪክ ነው፡፡ ኢህአዴግ በዚህ ወቅት በጦር ሜዳ ውሎ አቻ እንደሌለው ሊነግረን የሚፈልግ ይመስለኛል፡፡ ከጦርነቱ ጀብድ ባሻገር ግን የጦርነቱ ውጤት ምንድን ነው በማለት እንድንጠይቀው አይፈቅድም፡፡ ተጋዳላዮቹ ለምን ነበር ይህን ሁሉ ዋጋ የከፈሉት አዎን መልሱ ለእነርሱ ቀላል ሆኖም ይሆናል፣የተዋጋነው ደርግን ለመጣል ነው ሊሉን ይችላሉ፡፡

እርግጥ ነው ደርግ በህዝብ ልጆች ደም ቤተመንግስቱን የገነባ ጅላጅል አምባገነን ነበር፡፡አዲሶቹ ገዢዎቻችን ደርግን በመጣል ደርግን በስም ባይሆንም በግብር ከመሰሉ የደርግ ውድቀት ለህዝቡ እውን አልሆነም ማለት ነው፡፡ ለዚህም ይመስለኛል የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ የለውጡ ራስ ተደርገው ይታዩ የነበሩትን አቶ መለስ ዜናዊን‹‹መንግስቱ ኃይለማርያምን መሰልከኝ›› ያሉት፡፡ነጋሶ ቆይተውም ቢሆን በመለስና በመንግስቱ መካከል ልዩነት አለመኖሩን ተገንዝበዋል፡፡ አቀንቃኙ ቴዎድሮስ ካሳሁን(ቴዲ አፍሮ)ለለውጥ ያጎፈሩት አብዮተኞች ለቤተመንግስቱ አዲስ ከመሆናቸው ውጪ እናመጣዋለን ያሉትን ለውጥ አለማምጣታቸውን ስልጣንን ከጨበጡ 14 ዓመታት በኋላ ማቀንቀኑ አይዘነጋም፡፡በኢህአዴግና በደርግ መካከል ልዩነት አለመኖሩን በአስረጂነት ከምንጠቅሳቸው ድርሳናት መካከል‹‹ነጻነትን የማያውቁት ነጻ አውጪዎች›› የሚለው የአንዳርጋቸው ጽጌ መጽሀፍ ተጠቃሽ ነው፡፡

ኢህአዴጋዊያን በግንቦት ሃያ የሚቀሰቀስባቸው የበረሃ ትውስታ ለሰላማዊ ትግል ውጤታማነት የሚያስተላልፈው መልእክት በዜሮ ሊባዛ የሚችል ነው፡፡ ደርግ ከአፈሙዝ ውጪ የጨበጠውን ስልጣን የሚያስጠብቅበት የህዝብ መተማመኛ አልነበረውም እናም ኢህአዴጋዊያን ደርግን በሚገባው ቋንቋ በማናገር ስልጣኑን አሳጥተውታል፡፡ ጥያቄው አሁንስ ነው? የተጋዳላዮቹን የበረሃ ህይወት ስትመለከቱ ወደ ህሊናችሁ የሚመጣው ምንድን ነው? ኢህአዴግ ከብረት ውጪ የሚገባው ቋንቋ የለውም የሚሉ ሃይሎች ጥራኝ ዱሩ ማለታ ስለመጀመራቸው እየሰማን ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ የመጣበት መንገድ ሰላማዊ ባለመሆኑም የግንቦት ሃያ የጦርነት ዲስኩር እነዚህ ሃይሎች የጀመሩት ትግል ፍትሃዊ መስሎ እንዲታያቸው እንደማጣቀሻ ሊወስዱት ይችላሉ፡፡

በእኔ እምነት ኢህአዴግ በግንቦት ሃያ ሊየሳየን የሚፈልገው እውነታ ደርግን በመፈንገል ወንበሩን ስለ መውረሱ ብቻ ነው፡፡ ደርግን ማውገዝ ከደርግ የሚነጥለው ስለሚመስለው የወደቀውን ስርዓት በግንቦት ሃያ እየደጋገመ ይረግመዋል፡፡ መሬት ላይ ያለው እውነታ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በትግሉ ሜዳ አልፈው አራት ኪሎ የደረሱ አልያም የግንቦት ሃያ ፍሬ ነን የሚሉ በዚህ ወር ከደርግ በኋላ እየመሩት ስለሚገኘው ህይወት መጠየቅ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

ርዕይ የሌለው ግንቦት ሃያ ርዕይ ባለው ሌላ ግንቦት ሃያ እስካልተቀየረ ድረስ እነ ቀሽ ገብሩን እያስታወሱ እነ ብርቱካንን ማሳደድ አይቀሬ ይሆናል፡፡የግንቦት ሃያ ፍሬዎችም ስለ እነርዕዮት አለሙ የሚጠይቃቸውን ድምጽ እያፈኑ ስለቀሽ ገብሩ ብቻ ስናወራ ስሙን ማለታቸው ቅንጣት የይሉኝታ ስሜት አይፈጥርባቸውም፡፡ግንቦት ሃያ ላስከፈለው የህይወት ዋጋ ቦታ የሚሰጥ አካል አግኝቶ ቢሆን ቀኑን ሁላችንም የአገራችን ካርኒቫል ባደረግነው ነበር፡፡ነገር ግን ይህ ባለመሆኑ በመስከረም ሁለትና በግንቦት ሃያ መካከል ያለው ልዩነት ጠፍቶብን አስረጂ እንፈልጋለን፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# በሲዳማ ዞን ሙሰኞችን ለማጋለጥ የተጠራው ስብሰባ ተቀለበሰ

የሲዳማ ዞን አስተዳደር ‹‹ የመልካም አስተዳደር ችግርንና ሙሰኝነትን ለመዋጋት ›› በሚል ርዕስ በአለታ ወንዶ ከነዋሪዎች ጋር ለመወያየት በማሰብ በአደባባይ የጥሪ ወረቀት ይለጥፋል፡፡ ነገር ግን የስብሰባው ሰዓት እየተቃረበ በመጣበት ሰዓት በአደባባይ የተለጠፈው የጥሪ ወረቀት እንዲነሳ ይደረግና የኢህአዴግ ደጋፊ የሆኑ ሰዎች የጥሪ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

የተለጠፈው ወረቀት መነሳቱን ያላወቁና ስለ ከተማቸው መልካም አስተዳደር ችግርና ስለ ሰፈነው ሙሰኝነት የዞኑን አመራሮች ለማነጋገር የተዘጋጁት የአለታ ወንዶ ነዋሪዎች ስብሰባው የሚደረግበትን የሚሊኒየም አዳራሽ ከአፍ እስከ ገደፉ ይሞሉታል፡፡

ከስብሰባው መሪዎች አንዱ የሆኑት የሲዳማ ዞኑ አስተዳዳሪ አቶ ሚልዮን ማቲያስ በድንገት የድምጽ መነጋገሪያ መሳሪያውን በመጠቀም ‹‹በስብሰባው እንድትሳተፉ የጥሪ ደብዳቤ ከደረሳችሁ ሰዎች ውጪ ያላችሁ በሙሉ አዳራሹን ለቅቃችሁ እንድትወጡ ይህንን ባታደርጉ ግን ሁከት ለመፍጠር እንዳሴራችሁ በመንገር በፌደራል ፖሊስ በኃይል አዳራሹን ለቅቃችሁ እንድትወጡ አደርጋለሁ›› በማለቱ ህዝቡ ግርግር ከመፈጠሩ በፊት አዳራሹን ለቅቆ ወጥቷል፡፡ በአዳራሹ የቀሩት ጥቂት ሰዎች ዞኑ ምንም አይነት የመልካም አስተዳደርና የሙሰኝነት ችግር እንደሌለበት በመነጋገር ስብሰባውን ማጠናቀቁን የፍኖተ ነፃነት ምንጮች ገልጸዋል፡፡

የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጉዳዩን ለማጣራት ወደ ሲዳማ ዞን ብንደውልም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

# ወደ ዘዋይ የተወሰዱት የፖለቲካ እስረኞች አያያዝ አስጊ እንደሆነ ተጠቆመ

ወደዝዋይ የተወሰዱ የፖለቲካ እስረኞ በአስቸጋሪ ሆኔታ ውስጥ እንደሚገኙ የእስር ቤቱ ምንጮች ለፍኖተ ነፃነት ተናገሩ፡፡

የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ናትናኤል መኮንን ጨምሮ በቅርቡ ወደ ዘዋይ የተወሰዱት የፖለቲካ እስረኞች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ሁኔታው ያሳሰባቸው የእስር ቤቱ ምንጮች ለፍኖተ ነፃነት ጠቁመዋል፡፡

ምንጮቹ እደገለፁት ታሳሪዎቹ እጅግ በተጨናነቀ ሁኔታ ከመታሰራቸውም በላይ ጥራቱ ያልተጠበቀ ውሃ እንዲጠጡ እየተደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም ፅዳቱ ባልተጠበቀና ከአርባ ሰው በላይ በሚጠቀምበት መፀዳጃ ውስጥ እንዲጠቀሙ መደረጋቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡ የታሳሪዎቹ ሁኔታ ያሳሰባቸው እነዚሁ ምንጮች “መንግስት የታሳሪዎችን ደህንነት የመጠበቅ፣ በተቻለው አቅም ማረሚያ ቤቱን ለታራሚዎች ምቹ ማድረግና ጤናቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ የፖለቲካ በቀሉን በዚህ አይነት መንገድ መወጣት የለበትም” በማለት መንግስት የእርምት እንዲወስድ ጠይቀዋል፡፡

ዝግጅት ክፍላችን ስለሁኔታው ለመረዳት የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ናትናኤል መኮንን ባለቤት ወ/ሮ ፍቅርተን ጠይቆ እንደተረዳው አቶ ናትናኤል በተመሳሳይ ሁኔታ በመታሰራቸው ለጤናቸው እንደሚያሰጋ ተናግረዋል፡፡

ስለጉዳዩ የዘዋይ እስርቤት ሃላፊዎችን ምላሽ ለማካተት ያደረግነው ጥረት ስልላቸውን ባለማንሳታቸው አልተሳካም፡፡





የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የአዲስ አበባ ዞንን ለማጠናከር ባደረገው አጠቃላይ ግምገማ መሰረት ዞኑ አዳዲስ የምክር ቤትና የስራ አስፈፃሚዎችም መርጧል፡፡

የአዲስ አበባ ዞን እንቅስቃሴ አሁን ትግሉ ከሚከልገው ቁርጠኝነትና ከሚፈለገው የሰው ኃይልና የዕውቀት ቁመና አንፃር ድክመት ለመቅረፍ በፓርቲው ስኬታማ ስራ ተሰርቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በፓርቲው ሊ/መንበር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የሚመራ 12 አባላት ከብሔራዊ ምክር ቤት በመመልመልና የአጭር ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ሚያዝያ 13 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዞን ም/ቤት በማፅደቅ የኮሚቴ አባላቱ ሚያዝያ 20፣23 እና ግንቦት 4 ቀን በሁሉም የምርጫ ወረዳዎች በመዘዋወር ግምገማ አድርገዋል፡፡

በግምገማው የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ግንቦት 11 ቀን 2005 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዞን አዳዲስ የምክር ቤትና የስራ አስፈፃሚዎችም መርጧል፡፡ በተለይ የስራ አስፈፃሚ ምርጫው በዞኑ ምክርቤት ውስጥ የተሻለ የፖለቲካ ልምድና የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው አባላት ተወዳድረው በስራ አስፈፃሚነት ተመርጠዋል፡፡

በዚሁ መሠረትም አቶ ትዕግስቱ አወሉን የአዲስ አበባ ዞን ምክር ቤት ሊቀመንበር በማድረግ መመረጣቸውን ከአንድነት ፓርቲ የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67

# በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የአንድነት አባላትን የማሰር ዘመቻው እንደቀጠለ ነው

በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች ሚገኙ የአንድነት አባላትንና የአፋር ክልል የፍኖተ ነፃነት ተባባሪ ዘጋቢ እንደደረሰባቸው ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ፡፡

የአፋር ክልል የፍኖተ ነፃነት ተባባሪ ዘጋቢ በቅርቡ በክልሉ የአፋርና የሶማሌ ጎሳዎች መካከል በግጦሽ መሬት ምክንያት ለ3 ቀናት የዘለቀውን ግጭት ቦታው ድረስ መሄድ በሞባይሉ በመቅረፁ በክልሉ ፖሊሶች ለአንድ ቀን ከታሰረ በኃላ ግንቦት 12 ቀን 2005 ዓ.ም በሞባይሉ የቀረፃቸው መረጃዎች ተደምስሰው ሊለቀቅ ችሏል፡፡ ዘጋቢያችን በግጭቱ አራት የአፋር ተወላጆች ሞታቸውንና 14 ሰዎች መቁሰላቸውን አስመልክቶ መረጃ አድርሶን ነበር፡፡

በተያያዘ ዜና በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን ታች አርማጨሆ ወረዳ የአንድነት ፓርቲ የወረዳ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ተገኝ ሲሳይ ከሚያዝያ 19 ቀን 2005 ጀምሮ ከሳንጃ ከተማ በመንግስት የደህንነት ሃይሎች ታፍነው የደረሱበት ከጠፉ በኋላ ከሚያዝያ 26 ቀን 2005 ጀምሮ ወደ ጎንደር ከተማ 2ኛ ፖሊስ ጣቢያ መወሰዳቸው ታውቋል፡፡

አቶ ተገኝ እስከ አሁን በቤተሰቦቻቸውና በትግል አጋሮቻቸው እንዳይጠየዉ ተደርጓል፡፡ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የአቶ ተገኝ ሲሳይን መዝገብ ይዘዋል የተባሉት የጎንደር ከተማ 2ኛ ፖሊስ ጣቢያ መርማሪ የሆኑት ኢንስፔክተር ማረልኝ ጋር ቢደውልም "አቶ ተገኝ የሚባል እስረኛ የሚባል እስረኛ አላውቅም" በማለት ስለእስሩ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ተአሳውቀዋል፡፡

የቅርብ ቤተሰቦቻቸውና በጎንደር የሚገኙ የአንድነት ፓርቲ የዞን አመራሮች ለፍኖተ ነፃነት እንደገለፁት አቶ ተገኝን ለመጠየቅ በሄዱበት ወቅት ፖሊሶቹ "አቶ ተገኝ በብሔራዊ ደህንነት ማዕከል የታሰሩ የአደራ እስረኛ ናቸው ልናስጎበኛችሁ አንችልም" ተብለዋል፡፡

# ጸረ ሙስና የዝቋላ ብረታ ብረት ፋብሪካን አስተዳደር በምክር ማለፉ አነጋጋሪ ሆኗል

## -‹‹በ2.5 ሚልዮን ዮሮ የተገዛ ማሽን ያለ አገልግሎት ተቀምጧል›› ጸረ ሙስና ኮሚሽን

## - ‹‹ጸረ ሙስና ስለ እኛ ሪፖርት ማቅረቡን አናውቅም››የፋብሪካው አስተዳዳሪ አቶ ጥበበ አየለ

በዝቋላ ብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካ ንብረት አስተዳደር ከፍተኛ ሙስና መኖሩን አስመልክቶ የደረሳቸውን ጥቆማ በመንተራስ የጸረ ሙስና ኮሚሽን አጣሪዎች በፋብሪካው ምርመራ ሲያደርጉ ቢቆዩም የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አሊ ሱሌይማን ለፓርላማው አቅርበውት በነበረው የአስር ወራት የኮሚሽኑ ሪፖርት በዝቋላ ብረታ ብረት የታየው ክፍተት ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል በሚል ምክር ማለፋቸው በፋብሪካው እየተፈጸመ የሚገኘውን ብክነት በቅርበት የሚያውቁ ሰዎችን አስገርሟል፡፡

የፍኖተ ነፃነት ምንጮች እንደጠቆሙት ከሆነ ግልጽ ጨረታ ባልተደረገበት ሁኔታ 2.5 ሚልዮን ዩሮ ወጥቶባቸው የተገዙ የማምረቻ ማሽኖች ያለ አገልግሎት ተቀምጠዋል፡፡ ጸረ ሙስና ኮሚሽን በሪፖርቱ ከፍተኛ የምርትና የስራ ሰዓት ብክነት እንዲሁም ተመሳሳይ ችግሮች እንደሚስተዋሉ ከመጠቆም አልፎ ለፋብሪካው መሰረታዊ አገልግሎት ይሰጣሉ ተብለው የተገዙት ማሽኖች የሚፈለገውን አገልግት በመስጠት ላይ እንደማይገኙ ማረጋገጡን ይፋ አድርጓል፡፡

ለፋብሪካው ስራ አስኪያጅ አቶ ጥበበ አየለ በፍኖተ ነፃነት ተደውሎላቸው በስልክ አለ ስለሚባለው ከፍተኛ ሙስና እና ተያያዥ ችግሮች በሰጡት ምላሽ ‹‹በመጀመሪያ ደረጃ ጸረ ሙስና ኮሚሽን የእኛን ፋብሪካ በሚመለከት በፓርላማ ሪፖርት ስለማቅረቡ የማውቀው ምንም ነገር የለም፡፡ ምርመራ ተደርጓል መባሉም ከኛ እውቅና ውጪ ነው፡፡ ማሽኖቹን የገዛናቸው ግልጽ የሆነ ጨረታ በማውጣት ሲሆን አስፈላጊነታቸውም በፋብሪካችን ባለሞያዎች ታምኖበታል በዚህ ላይ ማሽኖቹ ያለ አገልግሎት አልተቀመጡም አስፈላጊውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ›› ብለዋል፡፡

ተመሳሳይ ጥያቄ የቀረበላቸው የፋብሪካው ኃላፊ አቶ በፍቃዱ ዘውዴ በበኩላቸው ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ተናግረዋል፡ ፡ የዝቋላ ብረታ ብረት ፋብሪካ በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኝ ሲሆን የተመሰረተው ከደቡብ አፍሪካው የብረታብረት አምራች ፋብሪካ (ISCOR)ብረት ለማምረት የሚያስችል ንጥረ ነገር ተገዝቶ በ1990 መገንባቱ አይዘነጋም፡፡

# የኢክስቴንሽን ባለሙያዎች ፖለቲካዊ ስራ እንዲሰሩ ታዘዙ

በአማራ ክልል የሚገኙ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የፖለቲካ ስራ እንዲሰሩ መታዘዛቸውን ለፍኖተ ነፃነት አስታወቁ፡፡

የግብርና ባለሙያዎቹ እንደሚሉት በቅርቡ ከክልል በወረደላቸው መመሪያ መሰረት ከሰለጠኑበት ሙያ ውጪ የገዢውን ፓርቲ ገፅታ የሚገነቡ የፖለቲካ ስራዎችን እንዲሰሩ ታዘዋል፡ ፡ "ከብቶቻቸውን ለማሳከም ወይም ሌሎች መንግስት ያመቻቸውን የነፃ አገልግሎቶችን ፈልገው የሚመጡ አርሶአደሮችን አገልግሎቱ የሚሰጣቸው ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ካለ ብቻ እንደሆነ እንድናሳምናቸው ታዘናል" የሚሉት የግብርና ባለሙያዎቹ የሚያስገመግማቸው የስራ አፈፃፀም ዋናው ሙያዊ አገልግሎታቸው ሳይሆን የፖለቲካ ስራው መሆኑ እንዳሳሰባቸው ለፍኖተ ነፃነት ተናግረዋል፡፡

በቅርቡ በትምህርት ምክንያት ወደ ደብረዘይት የመጣና ስሙ እንዳይገለፅ የጠየቀው የግብርና ባለሙያ እንደሚያስረዳው መንግስት በተለይ በአማራ ክልል አርሶ አደሩን ሙሉ ለሙሉ በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ከማሰሩም በላይ ከኢህአዴግ አመለካከት ውጪ ለመሆን የሚሞክሩትንና አስተዳደራዊ በደል ደረሰብን ብለው ቅሬታ የሚያቀርቡትን አርሶአደሮች የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዳያገኙ እያደረገ ነው፡፡

በተያያዘ ዜና በአማራ ክልል የሚገኙ አርሶ አደሮች ከአቅማቸው በላይ ገንዘብ እንዲያወጡ እየተገደዱ መሆናቸውን በክልሉ የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡ ባለሙያዎቹ እንደሚሉት አርሶ አደሮቹ ከ550 እስከ 700 ብር እንዲያወጡና ማዳበሪያም በግዳጅ እንዲገዙ እየተደረገ ነው፡፡ የየአካባቢው የመንግስት ሀላፊዎች ይህን ተፈፃሚ የማያደርጉ አርሶአደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸው እንደሚቀማ ማስፈራራታቸው ገበሬው ወደ አራጣ ብድር ለመግባት እየተገደደ መሆኑ ታውቋል፡፡ የግብርና ባለሙያዎቹ ትእዛዙ መሬታቸውን አከራይተው በሚጠቀሙ አርሶ አደሮች ላይ ተፈፃሚ እየተደረገ መሆኑ መመሪያውን አስገራሚ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

**ፍኖተ ነፃነትን በገንዘብ ይደግፉ ለተጨማሪ መረጃ +251-933-89-17-66 , +251-933-89-17-67**

አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት
የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል
የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል
እርስዎም ፦

. ኩፖን በመግዛት

. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት

. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ
አጋርነትዎን ያረጋግጡ

ለተጨማሪ መረጃ
0933-89-17-66 እና
0933-89-17-67 ይደውሉ
udjparty@gmail.com

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ
በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!

ፍኖተ ነፃነት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ